# የአርሊንግተን ካውንቲ የህጻናት
# አገልግሎቶች ሕግ

በስጋት ላይ ያሉ ወጣቶችና ቤተሰቦች አጠቃል የአገልግሎቶች ሕግ ለልጅዎ እና ለቤተሰብዎ አገልግሎቶቹን በምትቀበሉበት ወቅት የተወሰኑ መብቶችን እና ጥበቃዎችን ይሰጣቸዋል።

እነዚህ የሥነ ሥርአት ጥበቃዎች አሁን በስራ ላይ ባለው የግዛት ወይም የፌደራል ሕግ ስር (ለምሳሌ፡ የልዩ ትምህርትና የማደጎ እንክብካቤ ሕግ) በየትኛውም ሌሎች የማሻሻያ/ ምርመራ ሥነ ሥርዓቶች ስር አያልፉም።

1. የቤተሰብ ጥናትና እቅድ ዝግጅት ቡድኑ የግል የቤተሰብ አገልግሎቶች እቅዱን ጥናት፣ እቅድ ማዘጋጀትና ትግበራ ከመጀመሩ በፊት ለእርስዎ የጽሁፍ ማስታወቂያ መስጠት አለብዎ።
2. ማስታወቂያ በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ማግኘት አለብዎ።
3. የትኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚስጥር መረጃዎን ለሌሎች ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ከመግለጹ በፊት እርስዎ የጽሁፍ ፍቃድዎን መስጠት አለብዎ (መገለጹ በህግ ካልተጠየቀ ወይም በፍርድ ቤት ካልታዘዘ በቀር)።
4. የግል የቤተሰብ አገልግሎቶች ዕቅድ መተግበር ከመቻሉ በፊት እርስዎ የጽሁፍ ፍቃድዎን መስጠት አለብዎት። (ማስታወሻ: አገልግሎቶቹን ያለ እርስዎ የጽሁፍ ፍቃድ መቀጠል የሚያስፈልግባቸው ልዩ ሁኔታዎች አሉ)።
5. በግል የቤተሰብ አገልግሎቶች ዕቅድ ስር የተካተቱ አገልግሎቶችን የመከታተል ኃላፊነት ተሰጥቶት የሚመደብ ሰው ይኖርዎታል። ይህ ሰው የጉዳይ ስራ አስኪያጅ ተብሎ ይጠራል።
6. እንደ ወላጅነትዎ ልጅዎን በተመለከተ በሚካሄዱ በሁሉም የቤተሰብ ጥናትና እቅድ ዝግጅት ቡድን ስብሰባዎች ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ። የጊዜ ሰሌዳ በተያዘለት ስብሰባ ላይ መገኘት የማይችሉና ይህን ከስብሰባው መካሄድ አስቀድመው ለጉዳይ ስራ አስኪያጅዎ የማያሳውቁ ከሆነ በስብሰባው ላይ የመገኘት መብትዎን እንደተዉ ይቆጠራል። በቡድኑ ስብሰባዎች ላይ ሌላ የቤተሰብዎ አባልን፣ ጓደኛዎን፣ ጠበቃዎን ወይም ድጋፍ ሰጪዎ ሰውን ይዘው ሊገኙ ይችላሉ።
7. የቤተሰብ ጥናትና የእቅድ ዝግጅት ቡድን ውሳኔ እንዲመረመርልዎ ሊጠይቁ ይችላሉ። ለዚህ የመጀመሪያው ደረጃ የጉዳይ ስራ አስኪያጅዎን ማነጋገር ነው። በዚህ ችግሩን መፍታት ካልቻሉ የምርመራ ጥያቄዎን በማህበረሰብ ፖሊሲና አስተዳደር ቡድን ለሚሾመው የCSA የአስተዳደር ቡድን በጽሁፍ ሊያቀርቡ ይችላሉ። የአስተዳደር ቡድኑ ለጥያቄዎ በጽሁፍ መልስ ይሰጥዎታል። በቡድኑ ውሳኔ የማይስማሙ ከሆነ ለማህበረሰብ ፖሊሲና አስተዳደር ቡድን ይግባኝዎን ሊያቀርቡ ይችላሉ።
8. ስለ እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ የተመለከተ መረጃ በሌላ መልኩ ካልጠየቁ በቀር በሚስጥር ይያዛል።
9. መዝገቦችዎን የማየት፣ የመመርመር እና ኮፒያቸውን የመውሰድ መብት አሉዎት (በህግ ካልተከለከሉ በስተቀር)። ስለ እነዚህ መዝገቦች የተመለከተ ማብራሪያ ሊሰጥዎት ይችላል።
10. የተሳሳተ፣ ያልተሟላ ወይም አሳሳች እንደሆነ የሚያምኑበትን በመዝገብ ውስጥ የተካተተ መረጃን በአጠያያቂው መዝገብ ስር በማህደር ውስጥ የሚመር የጽሁፍ መግለጫ በመስጠት ሊቃወሙ ይችላሉ።

ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉዎ እባክዎ የጉዳይ ስራ አስኪያጅዎን ወይም የኤጀንሲውን የግንኙነት ሙያተኛ ያነጋግሩ።